ምኅዳር በስቱድዮ እና ምኅዳር በአዳማ

ስየ አብርሃ

እሁድ ነሐሴ 10 ቀን 2001 ዓ.ም. አንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትሕ ፓርቲ (አንድነት) በጠራው ሕዝባዊ ስብሰባ እንዲገኙ ከተጋበዙት የመድረክ ለዴሞክራስያ ምክክር በኢትዮጵያ (መድረክ) አባላት አንዱ በመሆን ወደ አዳማ ሄጄ ነበር። እንደ እኔ ሁሉ ደ/ር ነጋሶ ጊዳዳ፣ ፕሮፌሰር በየነ ጴጥሮስ፣ አቶ ቢንያም ሄራቦ እና አቶ ሃዲ መሐመድ በእንግድነት ተገኝተዋል። የመድረኩ አባል የኾኑ ፓርቲዎች በሚጠሩዋቸው ሕዝባዊ ስብሰባዎች እና ጉባኤዎች ስገኝ የመጀመርያየ አይደለም። በተናጠል የሚደረግ ትግል ብዙ ርቀት እንደማያስኬድ፤ ጊዜው ፓርቲ የሚያደርሰውን አፈና ተቋቁሞ ውጤታማ ስራ መስራት የሚቻለው ትግልን አስተባብሮ በመሄድ ብቻ መኾኑን ከመገንዘብ የተፈጠረ መድረክ እንደመሆኑ የመድረኩ አባል ፓርቲዎች በሚጠሩዋቸው ሕዝባዊ ስብሰባዎች ስገኝ ቆይቻለሁ ወደ ፊትም እቀጥልበታለኹ።

የአንድ ፖለቲካዊ ፓርቲ እንግዳ ኾኜ በአዳማ ስገኝ ይህ የመጀመርያየ አይደለም። መጋቢት ወር 1992 ዓ.ም. ዓሥረኛው የኦሮሞ ሕዝብ ዴሞክራስያዊ ድርጅት (ኦህዴድ) ምሥረታ በዓል ሲከበር የወቅቱ የድርጅቱ ሊቀ መንበር አቶ ኩማ ደመቅሳ ጋብዞኝ በበዓሉ ላይ ተገኝቻለኹ። በአዳማ የቀደሙት የትግል ጓደኞቼ - እነ አቶ ኩማ ደመቅሳ እና እነ አቶ አባዱላ ገመዳ - ያኔ የነበረውን የወዳጅነት አቀባበል ያደርጉልኛል ብየ አልጠበቅኹም። ይኹንና ከፓርቲያቸው ኦህዴድ/ ኢህአዴግ ጋራ ባለ የፖለቲካ ልዩነት ምክንያት ነሐሴ 10 ቀን አንድነት በጠራው ስብሰባ ለመገኘት በአዳማ ማዘጋጃ ቤት የስብሰባ አዳራሽ ለተገኘነው እኔና ሌሎች ኢትዮጵያውያን የገጠመንን ዐይነት "መስተንግዶ" ያደርጉልናል ብለን ግን አልጠበቅንም ነበር።

አንድነት ሕጋዊ እውቅና የተሰጠው ኅብረ ብሔራዊ ፓርቲ መኾኑ ይታወቃል። ፓርቲው ሕዝባዊ ስብሰባውን ለመጥራት በጽሑፍ የሰፈረው ሕግ ካስቀመጠው ግዴታ በላይ እንዲያደርግ የተጠየቀውን ሁሉ አሟልቶ፣ ፈቃዱን ከሰጠው የከተማው መስተዳደር አደራሹን እንዲጠቀም ተፈቅዶለታል። ስብሰባውን የጠራው አንድነት ፓርቲ እንደመሆኑ መጠን በዚህ ዳስ ውስጥ ለተጠራው የፖለቲካ ድግስ ባለቤቱ ፓርቲው ራሱ እንጂ አህዴድ ወይም ሌላ ሊኾን እንደማይችል አንድ እና ሁለት የለውም።

ስብሰባው እንደተጀመረ እንኳን ደኅና መጣችሁ በማለት የተያዘውን ፕሮግራም ያስተዋወቁት አቶ ብሩ ብርመጂ ናቸው። አቶ ብሩ የአንድነት ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባል፣ በሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት የቢሾፍቱ አካባቢ ሕዝብ ተመራጭ ሲሆኑ ፈቃድ ማስገኘቱን ጨምሮ ለዚህ ስብሰባ ዝግጅት ሲያስተባብሩ ከከረሙት የአንድነት ፓርቲ ኃላፊዎች አንዱ ናቸው። በመክፈቻ ንግግራቸው፣ ለተደረገው ዝግጅት የአዳማ ከተማ መስተዳደር ያደረገውን ትብብር እጅግ በማመስገን ስብሰባው የተጠራበትን ዓላማ አስመልክተው መሪ ንግግር እንዲያደርጉ የአንድነት ፓርቲ ተቀዳሚ ም/ሊቀ መንበር ኢንጂነር ግዛቸው ሺፈራውን ወደ መድረኩ ጋበዙ።

ኢንጂነር ግዛቸው በጽሑፍ ያዘጋጁትን ንግግር ሲጀምሩ ከአዳራሹ በስተጀርባ ከተቀመጡት በኩል የማጉረምረም ድምፅ ተሰማ። ብዙም ሳይቆይ ወደ ጩኸት እና ፉጨት ተሸጋገረ። ድርጊቱ ስብሰባውን ለመረበሽ የታቀደ ፕሮግራም መኾኑ ግልጽ እየኾነ ሄደ። ኢንጅነሩ ንግግራቸውን ለመቀጠል ቢሞክሩም ሰዎቹ ከተቀመጡበት ተነሥተው ወደ መድረኩ በመጠጋት ኹኔታውን በእርጋታ ሲከታተል የነበረውን ተሰብሳቢ በማወካቸው ንግግራቸውን ለማቋረጥ ተገደዋል። ሰዎቹን ለማረጋጋት ቢሞክርም ባለማሳካቱ ኢንጅነር ግዛቸው፣ "ሕግና ሥርዐት ተከትለን የአዳማውን ስብሰባ ለማድረግ ጥረት ብናደርግም ኢህአዴግ ይህንን እንድናደርግ ስላልፈቀደ ስብሰባውን ለማቋረጥ ተገደናል" በማለት ስብሰባውን ዘጉ። ስብሰባውን ማወክ ዓላማቸውን አድርገው የመጡት ሰዎች በዚህ ያልተጠበቀ ኹኔታ የልባቸው ስለደረሰ ደስታቸውን በጭብጨባ ገልጸዋል። ከኢህአዴግ የተለየ አመለካከት ያለውን የአንድ ኢትዮጵያዊ ፓርቲ አመለካከት ለማስተዋወቅ ሕግንና ሥርዐትን አክብሮ የተጠራን ስብሰባ በማወክ እንዳይካሄድ ማድረግ እንደስኬት ተቆጠረና ጭብጨባ ተቸረው። ልቡና ላለው ሰው ግን በእጅጉ አሳፋሪ ድርጊት ነው።

አንድነት ኅዳር 17 ቀን 2001 ዓ.ም. በአዲስ አበባ በጠራው የመጀመርያ ሕዝባዊ ስብሰባ ማግስት የፓርቲው ሊቀ መንበር ወ/ሪት ብርቱካን ሚዲቅሳን በዳግመኛ እስር መነጠቁ ይታወቃል፡፡ ከዚያ ወዲህ አዲስ አበባ ላይ ሕዝባዊ ስብሰባ ለማካሄድ ቢጠይቅም አሁን ድረስ ፈቃዱን ለማገኘት አለመቻሉም ይታወቃል፡፡ ይህ በዚህ እንዳለ አዳማ ላይ የማዘጋጃ ቤቱን አዳራሽ ተጠቅሞ ስብሰባውን እንዲያካሂድ መፈቀዱን ስሰማ "ይህ ነገር የእውነት ነው?" ማለቴ አልቀረም፡፡ በዚሁ ጉዳይ ከአንድነት መሪዎች ጋራ አንዳንድ የቀልድ ቃላት የተወራወርንበት ኹኔታም ነበር፡፡ አቶ ብሩ ብርመጂ የከተማውን መስተዳደር እጅግ አድርገው ሲያመሰግኑ ስሰማ ውስጤ "መጨረሻውን ያሳየን" ማለቱ አልቀረም፡፡ በዙም ሰይቆይ የሆነው ሆነ፡፡ በምርጫ 97 ወቅትስ ቢሆን ግንቦት ሰባት ቀን በመጨረሻው ሰዓት ላይ (ማታውኑ) አይደለም ጉዱ የወጣው፡፡

ኢንጅነር ግዛቸው ለመናገር ያሰቡትን የመስማት ዕድሉ ተነፍጎናል፡፡ ለማድመጥ ከቻልናቸው የመጀመርያዎቹ ዓረፍተ ነገሮች እንደተገነዘብኹት ም/ሊቀ መንበሩ መጀመርያ ላይ ሊናገሩበት ያሰቡት ጉዳይ የአገራችን ፖለቲካዊ መኅዳር በሚመለከት ነበር፡፡ በዚህ ጉዳይ ዙርያ በገዢው ፓርቲ እና በተቃዋሚ ፓርቲ ተወካዮች መካከል የስቱድዮ ውስጥ ክርክር ተካሂዶ ከፊሉ በቴሌዥን ቀርቦልናል፡፡ የኢህአዴግ ተወካዮች የፖለቲካ ምኅዳሩ አለመጥበቡን እየተቀባበሉ ሲደስኩሩልን፣ በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ውስጥ ተዘረጉ ያሏቸውን አሰራሮች እና ሕጎች "ማሳያ ይኹኑላችኹ" ሲሉን አድምጠናል፡፡ አቶ መለስ በያዝነው ዓመት ሰኔ ወር ላይ በሰጠው ጋዜጣዊ መግለጫ "...ባለፉት አራትና አምስት ዓመታት የዴሞክራሲያዊና ፖለቲካዊ ትግል ሕጎችን ዓለም አቀፍ ደረጃ በጠበቀ አኳኃን ለማሻሻልና ለማዳበር ከፍተኛ ጥረት ተደርጓል፡፡ ..ያስቀመጥናቸው የዴሞክራስያዊ ፖለቲካዊ ትግል ሕጎች ዓለም አቀፍ ደረጃውን የጠበቁ ዴሞክራስያዊ ...የፖለቲካዊ ምኅዳሩን በየትኛው የዳበረ ዴሞክራሲ ባለው አኳኃን ዳር ድንበሩን የለዩ ሕጎች ናቸው" ብሎን ነበር፡፡ በሰቱድዮ እና በቢሮ ሆነው መግለጫ የሚሰጡት የኢህአዴግ መሪዎች የሚሉት እና እነሱ "አባል" "ፎረም" እያሉ የሚጠሩዋቸው እና ብዛታቸው ሚልዮን ቤት ደርሰዋል የሚባልላቸው "ቪጂላንቴዎች" የሚሰሩት ለየቅል መሆኑን አዳማ አሳይታለች፡፡ አንድ ፖለቲካዊ ክንዋኔ ብዙ ሰዓታት ከፈጀ ዲስኩር በላይ ጮኾ ይናገራል፡፡ በአገራችን ያለው የፖለቲካ ምኅዳር ለመጥበቡ ኢንጂነሩ ሊገልጹ ከሚችሉት ቃላት በበለጠ የኢህአዴግ ተግባር ስለገለጸላቸው ድካም ቀረባቸው እንጂ ስራ ተሰናከለባቸው ለማለት አይቻልም፡፡

ከዚሁ የአዳማው ስብሰባ ቀደም ብሎ ሰኔ 21 ቀን 2001 ዓ.ም. አንድነት የጠራው ስብሰባ ደብረ ማርቆስ ላይ፣ በጥር ወር ዓረና ትግራይ ለዴሞክራሲና ለሉዐላዊነት (ዓረና) የጠራው ስብሰባ መቀሌ ላይ ተካሂደው ነበር፡፡ በእነዚህ ከተሞች ኢህአዴግ ስብሰባዎቹን ለማሰናከል ተመሳሳይ ሙከራዎች አድርጎ እንደነበር ከወጡት መግለጫዎች ለመገንዘብ ችለናል፡፡ በሁለቱም ከተሞች ስብሰባ ለማካሄድ ተፈቅዶላችኋል ቢባልም ፓርቲዎቹ መኪና ተከራይተው በድምፅ ማጉያ የስብሰባ ጥሪ ሲያደርጉ በትራፊክ ፖሊስ ተከልክለዋል፡፡ በመቀሌማ ከዚያ በኋላ "ሕግ ወጥቷል" እየተባለ ነው፡፡

እንደአዳማው ሁሉ ዓረና በጠራው ስብሰባ ላይም የህ.ወ.ሓ.ት./ኢህአዴግ ባለስልጣናት ፈቃዱን ከሰጡና አዳራሹን ካከራዩ በኋላ ወደ ስብሰባው በገቡት የፓርቲው ካድሬዎች እና አባላት በኩል ስብሰባውን በማወክ እንዳይካሄድ ለማድረግ ከፍተኛ ጥረት አድርገው እንደነበረ ሂደቱን አስመልክቶ ዓረና ካወጣው ይፋዊ መግለጫ ለመገንዘብ ችለናል፡፡ የመቀሌው ከአዳማው የሚለየው ነገር ቢኖር ተሰብሳቢዎቹ ሁከት ፈጣሪዎቹን "ጥያቄ ካላችኹ በሥነ ሥርዐት ጠይቁ፣ ጥያቄ ከሌላችሁ ደግሞ እንደሌሎቻችን የሚሰጠውን መግለጫ አዳምጡ እንጂ አትረብሹን፡፡ እኛ እንደኾነ ለመስማት እና ለመወያየት እንፈለጋለን" በማለት ችግር ፈጣሪዎቹን አደብ እንዲገዙ ማስገደዳቸው ነው፡፡ ደብረ ማርቆስ ላይ መጀመርያ ላይ እንቅፋት ከመፈጠራቸው በቀር ወደ ውስጥ ዘልቀው ስብሰባውን ለማወክ አልደፈሩም፡፡

ውጤቱ ከቦታ ቦታ ይለያይ እንደሆነ እንጂ የኢህአዴግ ስልት ግን ከሞላ ጎደል ወጥነት ያለው ለመሆኑ ከነዚህ ምሳሌዎች ለመገንዘብ ይቻላል፡፡ ሰበብ እየፈጠረ ፈቃድ ይከለክላል፤ ያዘገያል፡፡ ፈቃድ ሰጥቶ ሲያበቃ ሕዝቡ ስለ ስብሰባው እንዳያውቅ የማስተዋወቁን ስራ ያስተጓጉላል፡፡ ይህ ሁሉ ታልፎ ስብሰባው ሲጀመር ደግሞ የስብሰባው ሂደት እንዲታወክ

ያደርጋል። "ስብሰባ አልተከለከለም" ለማለት ፈቃድ ከሰጡ በኋላም ቢሆን ስብሰባው እንዳይሳካ ያደርጉና "ተቃዋሚዎች ሕዝባዊ ስብሰባ የማያደርጉት በራሳቸው ችግር እንጂ መንግስት በሚፈጥርባቸው ዕንቅፋት አይደለም" በማለት ይሣለቃሉ። አቶ መለስ ሰኔ ላይ በሰጠው ጋዜጣዊ መግለጫ "የፖለቲካ ውድድር ቀርቶ የእግር ኳስ ጨዋታም ቢሆን የራሱ ህግ አለው። በእግር ኳስ እጅና እግር እየተጠቀሙ ጎል ማግባት አይፈቀድም፤...ፖለቲካም ከዚህ በላይ ነው" ቢለንም በአንድ በኩል ዓለም አቀፍ ደረጃቸውን የጠበቁ ህጎች አሉን እየተባለ ወረድ ብሎ ደግሞ በእግር እና በእጅ ጎል ላስገባ እያለ እያስቸገረ ያለው እርሱ ራሱ የሚመራው ፓርቲ ነው።

ለዚህ መልሱ አንዳንድ ወገኖች እንደሚሉት "ለሰላማዊ ትግል አመቺ ሁኔታ የለም" ብሎ መድረኩን ለኢህአዴግ መልቀቅ ወይም እኛም እንደነሱ በእጃችንም በእግራችንም ጎል እናስገባ ማለት አይደለም። የአዳማዎቹ ሁከት ፈጣሪዎች እኛ ያልነው ካልኾነ ብለው በኀይል ወደ አዳራሹ መድረክ ሲመጡ በአዳራሹ ውስጥ የነበሩት የአንድነት ደጋፊዎች አይኾንም ብለው ሰዎቹን ለማቆም ቢሞክሩ ኖሮ ግርግር መፈጠሩ አይቀሬ ነበር። ከዚያ በኋላ "ነውጥ" በመፍጠር የሚከሰሰው ማን እንደሆነ መገመቱ አይከብድም። ምስጋና ይግባቸውና በአዳራሹ የተገኙት የአንድነት ደጋፊዎች የሞራል ገዢ መሬቱን ለቀው ራሳቸውን አዋኪዎቹ ወደ አወረዱበት ደረጃ አላወረዱም። የመቀሌ፣ የደብረ ማርቆስ እና የአዳማ ድርጊቶቹ ኢህአዴግ ሰላማዊ ትግሉን ከትጥቅ ትግሉ በላይ እየፈራው ስለ መሆኑ ግልጽ ማሳያዎች ናቸው። የተቃውሞ ኀይሎች መድረኩን እንደዚህ ምንችክ ብለው ይይዛሉ እንጂ ለኢህአዴግ አይለቁለትም።

ተቃዋሚ ፓርቲዎች ተስፋ ሳይቆርጡ ያቀዱትን ዳር ማድረስ፣ ዕንቅፋት አጋጠመ ብሎ ሙከራውን ከማቆም ዛሬም ነገም ለምንጊዜውም መደጋገሙ ይልመድባቸው። እርስ በርስ መተባበር እና ተሞክሯቸውን እየቀመሩ በስልት አህአዴግን መብለጥና መቅደም ይልመድባቸው፤ ሕዝቡም በሂደት በሰው ዳስ እየገቡ የሚያውኩትን ሰዎች መቀሌ ላይ እንደተደረገው "ከፈለጋችሁ በስነ ስርዓት የፖለቲካ ድግሱ ተካፋይ ሁኑ አለበለዝያ በሰው ዳስ ገብታችሁ አትበጥብጡ" ብሎ አደብ ያስገዛቸዋል።

ተቃዋሚ ፓርቲዎች ይኽን መድረክ የኢህአዴግ መሪዎች ስትዱዮ እና ቢሮ ውስጥ ኾነው አልጠበበም የሚሉት ምኀዳር ስለመኖሩ ደብረማርቆስ፣ አዳማ እና መቀሌ ላይ እንደተደረገው መሬት ወርደው መፈተሹን ሊቀጥሉበት ይገባል። የአገራችን ጉዳይ ያገባናል ብለን በመታገል ብዙ ችግር እና ፈተና ያለፍን ሰዎች እንደመኾናችን ኢህአዴግ ወደ ስብሰባው የሚልካቸውን "ቪጂላንቴዎች" ፈርተን በስብሰባዎች ከመገኘት ወደ ኋላ እንደማንልም ሊታወቅ ይገባል። ሕግን እና ሥርዐትን አክብሮ መሄድ ያባት ነው። ይህን አልፎ ጉዳት ቢደርስብን ግን ሐላፊው ኢህአዴግ እና እርሱ የሚመራው መንግስት መሆኑን የኢትዮጵያ ሕዝብና ዓለም አቀፉ ማህበረሰብ እንዲያውቅ እንፈልጋለን።

ነሐሴ 13/2001 ዓ.ም.

.....................................

አቶ ስየ አብርሃን በseabrag@gmail.com ማግኘት ይቻላል።